የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ዘጠንኛዓመትቁጥር 29 ሠመራ --- ሚያዚያ 4 ቀን 1997 ዓ.ም	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት	2nd Year No. 29 Samara , January 2005

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዞን አስተዳደርን ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ.....

ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 29/1998 ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዞን አስተዳደርን ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

መግቢያ

የብሔራዊ ክልሉን የቆዳ ስፋት መልክአ ምድራዊ አቀማመጥና የዘመናዊ መገናኛ ዘዴዎች ውስንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣

የአርብቶ አደሩን ኑሮ ዘላቂና በተሻለ መንገድ ለመምራት እና ለውጥ ለማምጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም ከወረዳዎች አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮችን አማክለው የሚከታተሉ የልማት ስራዎችን የሚያቀናጁ የሚያስተባብሩና ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚሰጡ አስተዳደራዊ አደረጃጀቶችን ማቋቋም ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣-

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት ተሻሽሎ በወጣው ሕገ መንግስት አንቀጽ 47/3/ (ሀ) እና በአንቀጽ 43/1/ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዞን አስተዳደርን ማቋቋሚያ ስልጣንና ተግባራ መወሰኛ የክልል ም/ቤት አዋጅ ቁጥር 29/1998 ዓ.ም›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. ‹‹ሕገ መንግስት›› ማለት በ 1994 ዓ.ም የተሻሻለው አፋር ክልል ሕገ መንግስት ነው።
2. «ዞን» ማለት ለአስተዳደራዊ ምቹነትና ለሁለገብ የልማት ስራዎች ተፈፃሚነት ሲባል ከክልል መስተዳድር በታች ከወረዳ ስራ አስፈፃሚ አካላት በላይ የሚገኝ እና ከስሩ በህግ የተወሰኑ ወረዳዎችን ያቀፈ አካባቢያዊ የአስተዳደር እርከን ነው።
3. «የዞን አስተዳደር» ማለት በዋና አስተዳዳሪና በምክትል አስተዳዳሪ የሚመራ የአስተዳደር ጽ/ቤት ሆኖ የሚያገለግል አስፈፃሚ አካል ነው።

ክፍል ሁለት

አንቀጽ 3

የዞን አስተዳደር ስለማቋቋም

የሚከተሉት የዞን አስተዳደሮች በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁመዋል።

1. አውሲ ዞን
2. ኪልባቲ ዞን
3. ጋቢ ዞን
4. ፋንቲ ዞን
5. ኻሪ ዞን

አንቀጽ 4

አደረጃጀት

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙት ወረዳዎች ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት በዞን አስተዳደሮች ውስጥ ታቅፈዋል።

1. የአውሲ ዞን ወረዳዎች

   1. ዱብቲ ወረዳ
   2. አይሳኢታ ወረዳ
   3. አፋምቦ ወረዳ
   4. ኤሊዳአር ወረዳ
   5. ሚሌ ወረዳ
   6. ጭፍራ ወረዳ

2. የኪልባቲ ዞን ወረዳዎች

   1. ዳሉል

2. በራህሌ
3. ኮነባ
4. ኢራቢቲ
5. አፍዴራ
6. አብአላ
7. መጋሌ

3. የጋቢ ዞን ወረዳዎች

1. አዋሽ ፈንታሌ
2. አሚበራ
3. ቡሪሞዳይቱ
4. ገዋኔ
5. ዱለቻ
6. የአርንባ ልዩ ወረዳ

4. የፋንቲ ዞን ወረዳዎች

1. ያሎ
2. ቱሩ
3. ጉሊና
4. አውን
5. እዋ

5. የኽሪ ዞን ወረዳዎች

1. ተላላክ
2. ደዌ
3. ዳሊፋጌ
4. ሀደሌኤላ
5. ሰሙናገላእሎ

አንቀጽ **5**

ተጠሪነት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የዞን አስተዳደሮች ስራቸውን የሚያከናውኑት የክልሉን መስተዳድር በመወከል ይሆናል። ተጠሪነታቸውም ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት እና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።

አንቀጽ **6**

የዞን አስተዳደር አወቃቀርና አሰራር

1. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 43/1/ መሠረት ለተመጣጠነ ልማት ተፈፃሚነትና ለአስተዳደራዊ ስራ መቀላጠፍ አስፈላጊ ሆነው ባገኛቸው ዞኖች (የአስተዳደር አካባቢዎች) ተከፋፍሎ የተዋቀረ ነው።
2. በዚህ አዋጅ የተቋቋሙት ዞኖች የየራሳቸው ምክር ቤት አይኖራቸውም።

አንቀጽ 7

የዞን አስተዳደር ስልጣንና ተግባር

በዞን አስተዳደር የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል

1. የዞን አስተዳደሩ ውስጥ የሚካሄዱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይደግፋል ይከታተላል።
2. በተደራጀበት ዞን ውስጥ የሚገኙትን ወረዳዎች ስራ ያስተባብራል፣ ይደግፋል ይከታተላል።
3. በዞኑ ውስጥ የተቋቋሙትን ልዩ ልዩ ጽ/ቤቶችና ሌሎች ተቋማት ስራ ይደግፋል ይከታተላል ያስተባብራል።
4. ከአንድ ወረዳ በላይ ግልጋሎት የሚሰጡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተቋማት ያጋጠማቸው ችግር ቢኖር ይፈታል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል።
5. በተደራጀበት አካባቢ ሕግና ስርዓት መከበሩንና ሕዝቡ ሰላምና ደህንነት መጠበቁን ያረጋግጣል።
6. በክልሉ ም/ቤትና በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አማካኝነት የሚወጡ ፖሊሲ አዋጆች ደንቦች መመሪያዎች ውሳኔዎች በዞን ውስጥ በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋጋጣል።
7. በዞኑ ውስጥ የከተሞች ለማት የሚፋጠንበትን የንግድ ስራዎች የሚስፋፋበትን እና ኢንዱስትሪያዊ እድገት የሚረጋገጥበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።
8. የዞኑን ስራ እንቅስቃሴ እየተከታተለ ለርዕሰ መስተዳድሩ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል።
9. በርዕሰ መስተዳድሩና በመስተዳድር ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 8

የዞን አስተዳደር አመራር

1. የዞኑ አስተዳደር በክልሉ ም/ቤት የተቋቋመ ዞኑን የማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው የመስተዳድር ም/ቤቱንና የርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪ ጽ/ቤት ሆኖ የሚያገለግል አስፈፃሚ አካል ነው።
2. የዞኑ አስተዳደር በዋና አስተዳዳሪና በምክትል አስተዳዳሪ ይመራል።
3. እንደአስፈላጊነቱ የክለሉ ርዕሰ መስተዳድር ለአካባቢው ሰላምና ደህንነት እንዲሁም ለልማታዊ እንቅስቃሴ አጋዥ ለሚሆኑ ለሌሎች የስራ ኃላፊዎች ሹመት ይሰጣል።
4. የዞኑ አስተዳደር የራሱን የሆነ ጽ/ቤት ይኖረዋል።

አንቀጽ 9

ስለዞኑ ዋና አስተዳዳሪና ምክትል አስተዳዳሪ አሰያየምና የስራ ዘመን

1. የዞኑዋናአስተዳዳሪበክልሉርዕሰመስተዳድርአቅራቢነትበክልልምክርቤትይሾማል።
2. የዞኑምክትልአስተዳዳሪበክልሉርዕሰመስተዳድርይሾማል።

3. የዞኑዋናእናምክትልአስተዳዳሪዎቹየስራዘመንየክልሉርዕሰመስተዳድርየስራዘመንይሆናል።

አንቀጽ 10

የዞንዋናአስተዳዳሪስልጣንናተግባር

1. የክልሉንርዕሰመስተዳድርወክሎዞኑንያስተዳድራልስራውንበበላይነትየመራልይከታተላል።
2. በዞኑውስጥያሉትንየተለያዩቅርንጫፍ
   ጽ/ቤቶችንናተቋማትሁለንተናዊእንቅስቃሴይከታተላላስራቸውንያስተባብራልድጋፎችንይሰጣል፣፣
3. የአካባቢውንሰላምናደህንነትመጠበቅይቻልዘንድበዞንውስጥሕግናስርዓትእንዲያስከብሩየተቋቋሙትንየፀጥታናየፖሊስኃይሎ
   ችንበበላይነትየመራልይቆጣጠራል።
4. በዞኑውስጥየሚገኙየበታችአስተዳደርእርከኖችስራንያስተባብራልይከታተላል።
5. በሚያስተዳድረውዞንውስጥያለውንአጠቃላይየስራእንቅስቃሴእየተከታተለለርዕሰመስተዳድሩወቅታዊሪፖርትያቀርባል።
6. በርዕሰመስተዳድሩናበክልልመስተዳድር መ/ቤቱየሚሰጡትንሌሎችተግባራትያከናውናል።

አንቀጽ 11

የዞኑምክትልአስተዳደሪስልጣንናተግባር

1. ዋናአስተዳዳሪውበማይኖርበትወይምስራውንለማከናወንበማይችልበትጊዜተክቶይሰራል።
2. ም/አስተዳዳሪውበተለይበዞኑያሉትንየማህበራዊናኢኮኖሚያዊልማትስራዎችንይከታተላል።
   ያስተባብራልወቅታዊሪፖርትምለበላይኃላፊውያቀርባል።
3. በተጨማሪምበዋናአስተዳዳሪየሚሰጡትንሌሎችተግባራትያከናውናል።

አንቀጽ 12

ተጠሪነት

1. የዞኑአስተዳዳሪተጠሪነቱለክልሉመስተዳድር ም/ቤትአናለርዕሰመስተዳድሩይሆናል።
2. የዞኑምክትልአስተዳዳሪተጠሪነቱለዞኑአስተዳዳሪናለክልሉርዕሰመስተዳድርይሆናል።

አንቀጽ 13

የዞንአስተዳደር ጽ/ቤት

1. ዋናአስተዳዳሪውበዚህደንብመሠረትየተጣለበትንኃላፊነትለመወጣትበአንቀጽ 8/4/ በተገለፀውመሠረትየራሱየሆነ
   ጽ/ቤትይኖረዋል።
2. ጽህፈትቤቱተጠሪነቱለዞኑአስተዳዳሪውነው።
3. ጽህፈትቤቱለስራውአስፈላጊየሆኑክፍሎችናሰራተኞችይኖሩታል።

አንቀጽ 14

የስልጣንወሰን

የዞንአስተዳደርየስልጣንወሰንበዚህአዋጅአንቀጽ 7 ከተዘረዘረውበላይአያልፍም።

አንቀጽ 15

ደንብናመመሪያየማውጣትስልጣን

የክልሉመስተዳድርምክርቤትይህንአዋጅለማስፈፀምየሚረዱደንብናመመሪያዎችሊያወጣይችላል።

አንቀጽ 16

አዋጁየሚፀናብትጊዜ

ይህአዋጅበአፋርነጋሪትጋዜጣታትሞከወጣበትቀንጀምሮየፀናይሆናል።

ሠመራ

መስከረም --/1998 ዓ.ም

እስማኤልአሊሲሮ

የአፋርብሔራዊክልላዊመንግስት

ርዕሰመስተዳድር